በንግድና ቀጠናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን

# ነዳጅን ከኩባንያዎች በቀጥታ በመግዛት ለሚጠቀሙ ተቋማት የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 905/2014

ሰኔ 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(4) መሰረት የንግድና ቀጠናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ነዳጅን ከኩባንያዎች በቀጥታ በመግዛት ለሚጠቀሙ ተቋማት የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 905/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2 ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1/ "ተቋማት" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከኩባንያዎች በጅምላ በመግዛት በመንግሥት እና በግል ፕሮጀክቶች ላይ የሚሳተፉ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ናቸው፡፡

2/ "የተጠቃሚነት ፈቃድ" ማለት በዚህ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልተው ለሚመጡ ቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚሰጠው የጽሑፍ ፈቃድ ነው፡፡

3/ "ማከማቻ" ማለት ቀጥታ ተጠቃሚው የገዛውን የነዳጅ ውጤቶች የሚያከማችበት ታንከር ነው፡፡

4/ "ባለሥልጣን" ማለት የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ነው፡፡

5/ "ኩባንያ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት በጅምላ በመግዛት ለነዳጅ ማደያዎች እና ለቀጥታ ተጠቃሚዎች ለማሠራጨት ህጋዊ የሥራ ፈቃድ ያለው ኩባንያ ወይም ሰው ነው፡፡

6/ "ድርጅት" ማለት የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ነዉ፡፡

7/ "የነዳጅ ውጤት" ማለት ከተፈጥሮ ድፍድፍ ነዳጅ እና ከፔትሮሊየም ጋዝ፣ ባዮ-ፊውል ወይም ሴንቴቲክ ነዳጅን ከማጣራት ወይም ከማቀናበር የተገኘ ንፁህ ወይም አግባብ ባለው መንገድ የተደባለቀ የነዳጅ ውጤት ሆኖ ቤንዚንን፤ ኬሮሲንን፣ ናፍጣን፣ ቀላልና ከባድ ጥቁር ናፍጣንና የአውሮፕላን ነዳጅን ያካትታል፣

**አንቀጽ 3 የመመሪያው አስፈላጊነት**

ከፍተኛ የነዳጅ ውጤቶች ፍጆታ ያላቸው ተቋማትን ከጅምላ አከፋፋይ ኩባንያዎች በቀጥታ መግዛት የሚያስችላቸው የተጠቃሚነት ፈቃድ የሚሰጥበት፣ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

**አንቀጽ 4 የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በመንግሥት እና በግል ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ላይ የሚሳተፉ አካላት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የሆኑ የነዳጅ ቀጥታ ተጠቃሚዎች እና የነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 5 የባለሥልጣኑ ተግባራት**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1/ የቀጥታ ተጠቃሚ ተቋማት የሚያቀርቡትን የነዳጅ ውጤቶች ፍላጎት ተቋማቱ ከሚያከናውኑት ሥራ እና ከሚሰጡት የህዝብ አገልግሎት ጋር በማገናዘብ መጠኑን ይወስናል፣ የተጠቃሚነት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2/ ቀጥታ ተጠቃሚዎች የቀረበላቸውን የነዳጅ ውጤቶች ለተፈቀደው ዓላማ ብቻ ማዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

3/ የሪፖርት አቀራረብ ፎርማቶችን ይቀርፃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

4/ በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችንና ክልከላዎችን ያላከበረ ወይም የጣሰ ቀጥታ ተጠቃሚ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

5/ የነዳጅ ውጤቶች ማከማቻ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ያወጣል፣ በተቀመጠው መሥፈርት መሠረት መገንባታቸውን በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ይሰጣል፣

6/ ቀጥታ ተጠቃሚው ማሟላት የሚጠበቅበትን መስፈርት አሟልቶ ማቅረቡ ሲረጋገጥ ጥያቄ ላቀረበው አካል ሽያጭ እንዲፈጸምለት ለኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት፣ ለነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያ በደብዳቤ መፈቀዱን ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ 6 ቀጥታ የነዳጅ ተጠቃሚ ተቋማት ፈቃድ ለመጠየቅ ማቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች፤

1/ የነዳጅ ውጤቶችን ግዥ ፈቃድ ለመጠየቅ የሚፈልገውን የነዳጅ ውጤቶች መጠን፣ ዓይነት፣ ለምን ያህል ጊዜ እና ለምን አገልግሎት እንደሚውል በማስረጃ በማስደገፍ መግለጫ በተቋሙ የበላይ ሃላፊ ተረጋግጦ መቅረብ አለበት፣

2/ የመንግሥትም ሆነ የግል ድርጅት የተቋቋመበትን ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰነድ እና የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማቅረብ አለበት፣

3/ ከአንድ አመት እና ከዚያ በላይ በቋሚነት የሚጠቀም ከሆነ ወርሀዊ እና አመታዊ ፍጆታውን የሚያስረዳ ዝርዝር መርሐ ግብር ማቅረብ አለበት፣

4/ የሚፈልገውን የነዳጅ መጠን ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያ ጋር ውል ከመግባቱ በፊት ጥያቄውን ለባለሥልጣን መ/ቤቱ አቅርቦ ፈቃድ ማግኘት አለበት፣

5/ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ካገኝ በኋላ ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያ ጋር የስምምነት ውል በመግባት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ማቅረብ አለበት፣

6/ የሚጠየቀው የነዳጅ ውጤቶች ግዥ ፈቃድ ለፕሮጀክት ግንባታ ከሆነ ከአሠሪው ድርጅት ጋር የተደረገ የሥራ የስምምነት ውልና ሥራ ለመጀመር ዝግጅት ያጠናቀቀ ስለመሆኑ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት፣

7/ የነዳጅ ማከማቻው የኩባንያውን መስፈርት አሟልቶ የተገነባ ስለመሆኑ ማስረጃ ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያ ማቅረብ አለበት፣

8/ የአካባቢውን ማህበረሰብ ጤና እና የአካባቢውን ደህንነት ለአደጋ የማያጋልጥ ስለመሆኑ የደህንነት ማረጋገጫ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ አካል ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 7 የነዳጅ ውጤቶች ቀጥታ ተጠቃሚዎች ግዴታ

1/ የገዛውን የነዳጅ ውጤቶች ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ ማዋል አለበት፡፡

2/ የቀረበለትንና የተጠቀመበትን የነዳጅ ውጤቶች ዓይነትና መጠን፣ የተደራጀ መረጃ መያዝና በየ 3ወሩ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ማቅረብ አለበት፣

3/ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለሚያደርገው የመስክ ክትትልና ቁጥጥር ተገቢውን ትብብር ማድረግ አለበት፣

4/ የነዳጅ ውጤቶች ፍላጎቱ ከተፈቀደለት ጊዜ በላይ ቀጣይነት ያለው ከሆነ ፕሮጀክቱ አለማለቁንና የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ ጊዜያት በመጥቀስ የድጋፍ ደብዳቤና የማራዘሚያ ውል ፕሮጀክቱ ከማለቁ ከ3 ወር በፊት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ አቅርቦ ማስፈቀድ አለበት፣

5/ የተዋዋለው ሥራ ሲጠናቀቅ በ10 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ እና ለተዋዋለው የነዳጅ ውጤቶች አከፋፋይ ኩባንያ በማሳወቅ የነዳጅ ውጤቶች ተጠቃሚነቱን ማቋረጥ አለበት፣

6/ ቀጥታ ተጠቃሚው ከአንድ አከፋፋይ ኩባንያ በላይ ነዳጅ ለመግዛት ሲያስፈልገው በልዩ ሁኔታ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ማስፈቀድ አለበት፣

7/ ከባለሥልጣኑ የተጠቃሚነት ፈቃድ ለማግኘት በወር የነዳጅ ፍጆታው ከአንድ ነዳጅ ማመላለሻ ቦቴ ወይም ከ46,000 ሊትር በላይ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣

8/ ከላይ ከተጠቀሰው መጠን በታች የወር ፍጆታ ያላቸውና መስፈርቱን የማያሟሉ ተቋማት በወር ውስጥ ባሉት ሣምንታት ተከፋፍሎ በአቅራቢያቸው ካሉት ማደያዎች የዞን ወይም የከተማ አስተዳደር የንግድ ጽ/ቤቶችን እያስፈቀዱ መጠቀም ይችላሉ፣

9/ የቀጥታ ተጠቃሚው ነዳጁን የሚጠቀመው ለፕሮጀክት ሥራ ከሆነ ከፕሮጀክቱ ባለቤት በየዓመቱ በሥራ ላይ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 8 የነዳጅ ውጤቶች አከፋፋይ ኩባንያ ግዴታ

1/ ከቀጥታ ተጠቃሚው ጋር ውል ከመፈጸሙ በፊት የተዘጋጀውን የነዳጅ ውጤቶች ማከማቻ ታንከር በአካባቢው ብክለትና ብክነት የማያደርስ እና የኩባንያውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፣

2/ ቀጥታ ተጠቃሚው ሥራ ለመጀመር የሚያስችል በቂ ዝግጅት ያደረገ መሆኑን ሳያረጋግጥ ለቀጥታ ተጠቃሚው የነዳጅ ውጤቶችን ማቅረብ የለበትም፣

3/ ለቀጥታ ተጠቃሚው ያከፋፈለውን የነዳጅ መጠንና ዓይነት በየ3ወሩ ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፣

4/ ማንኛውም ኩባንያ ከቀጥታ ተጠቃሚ ጋር ውል መግባት ያለበት በፕሮጀክቱ የውል ዘመን ብቻ ነው፣

5/ ከቀጥታ ተጠቃሚ ጋር ያደረጉት የስምምነት ውል በተቋረጠ በ10 ቀን ወስጥ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 9 የነዳጅ ቀጥታ ተጠቃሚ ተቋማት አስተዳደራዊ ቅጣት

1/ ማንኛውም ቀጥታ ተጠቃሚ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ግዴታዎችንና ክልከላዎችን ባለማክበርና የነዳጅ አጠቃቀሙን በየ3ወሩ ሪፖርት የማያደርግ ከሆነ ወይም የሚላኩ ተቆጣጣሪዎች የሚጠይቁትን መረጃ ለመስጠት የማይተባበር ከሆነ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣

2/ ማንኛውም ተጠቃሚ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ድጋሚ ተመሳሳይ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ፣ የተፈቀደለትን የነዳጅ ውጤቶች ከተፈቀደለት ዓላማ ውጭ የተጠቀመበት እንደሆነ፣ የተሰጠውን የፈቃድ ጊዜ በማሳለፍ ሲጠቀም የተገኘ እንደሆነ፣ ባስፈቀደው ፕሮጀክት ስም የነዳጅ ውጤቶች አውጥቶ ላልተፈቀደለት ፕሮጀክት ሲጠቀም የተገኘ ከሆነ የጥፋቱን ክብደትና ያደረሰውን ጉዳት በማየት የነዳጅ ውጤቶችን እንዳይጠቀም ይታገዳል፣ የተሰጠው የተጠቃሚነት ፈቃድ ይሠረዛል፣ለህግ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

3/ በዚህ መመሪያ የተሰጡ አስተዳደራዊ ቅጣቶች በወንጀልና በፍትሐብሔር ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ከመሆን አያስቀርም፡፡

## አንቀጽ 10 የነዳጅ ውጤቶች አከፋፋይ ኩባንያ አስተዳደራዊ ቅጣት

1/ ማንኛውም የነዳጅ ውጤቶች አከፋፋይ ኩባንያ በየወሩ ሪፖርት ያማያደርግ ከሆነ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣

2/ ማንኛውም የነዳጅ ውጤቶች አከፋፋይ ኩባንያ የፅሁፍ ማስጠንቀቅያ ተሰጥቶት ድጋሚ ተመሳሳይ ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፣ ላልተፈቀደለት ቀጥታ ተጠቃሚ የነዳጅ ውጤቶችን የሸጠ እንደሆነ፣ ሥራ ባቆሙ ፕሮጀክቶች ስም የነዳጅ ውጤቶችን ከማከማቻ ወጪ ያደረገ እንደሆነ፣ ለፕሮጀክቱ ከተፈቀደለት የነዳጅ ውጤቶች መጠን በላይ የሸጠ እንደሆነ፣ እንደ ጥፋቱ ክብደትና ያደረሰው ጉዳት እየታየ ከነዳጅ ቀጥታ ተጠቃሚ አቅራቢነት ይታገዳል፣ ፈቃዱም እንዲሰረዝ ይደረጋል፣

3/ በዚህ መመሪያ የተሰጡ አስተዳደራዊ ቅጣቶች በወንጀልና በፍትሐብሔር ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ከመሆን አያስቀርም፡፡

## አንቀጽ11 የመተባበር ግዴታ

ተቆጣጣሪው አካል ይህን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውና በተለየ ሁኔታ ድጋፍ ሲጠይቅ የአካባቢው ፖሊስ እና የፍትህ አካላት መተባባር አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 12 ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ህጎች

በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የወንጀል፣ የፍትሐ ብሔር እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 13 ተፈፃሚነት ስለ የማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 14 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከሰኔ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አቶ ገ/መስቀል ጫላ**

**የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር**

**አዲስ አበባ**